ውድ አንባቢ፦ይህች ትንሽ መጽሐፍ የተዘጋጀችው መጽሐፍ ቅዱስ (ቶራህ፥ ዘቡር፥ ኢንጅል) እና ቁርአን ከአብርሃም ስለተወለዱት ሁለት ልጆች የሚሉትን እንድታነብና እግዚአብሔርም በአብርሃም ዘር በኩል ለአንተ ያደረገውን እንድትረዳ ነው።

«የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶቹ የተወሰዱት ከአሮጌው ትርጉም ነው።»

«የቁርአን ጥቅሶች የተወሰዱት በ38 ኛው ዘመን ከታተመው የቁርአን መጽሐፍ ነው።»

## 1. እግዚአብሔር ከአብርሃም ጋር የገባው ቃል ኪዳን

**ይህንን አስመልክቶ መጽሐፈ ሕግጋቱ ያሠፈረው ምን አለው?**

አብርሃም የሰባ አምስት ዓመት አዛውንት እያለ እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ቃል ኪዳን እንዲህ ሲል መሠረተ፦

> «ከአገርህ ከዘመዶችህም ከአባትህም ቤት ተለይተህ እኔ ወደማሳይህ ምድር ውጣ። ታላቅ ሕዝብም አደርግሃለሁ፥ እባርክሃለሁ፥ ስምህንም አከብረዋለሁ፤ ለበረከትም ሁን፤ የሚባርኩህንም እባርካለሁ፥ የሚረግሙህንም እረግማለሁ፤ የምድር ነገዶችም ሁሉ በአንተ ይባረካሉ። አብራምም እግዚአብሔር እንደነገረው ሄደ፤ ሎጥም ከእርሱ ጋር ሄደ፤ አብራምም ከካራን በወጣ ጊዜ የሰባ አምስት ዓመት ሰው ነበረ» (ኦሪት ዘፍጥረት 12፡1-4)።

**ቁርአን ውስጥ ያለውንስ ብናነብ ምን ይላል?**

ቁርአን እግዚአብሔር ከአብርሃም ጋር የገባውን ቃል ኪዳን አልያዘም።

## 2. የእስማኤል መወለድ

**ስለዚሁ በመጽሐፈ ቶራኽ የተጻፈ ምን ይኖራል?**

እስማኤል ከአጋር የተገኘ ልጅ ነው፦

> «የአብራም ሚስት ሦራ ግን ለአብራም ልጅ አልወለደችለትም ነበር፤ ስምዋ አጋር የተባለ ግብፃዊት ባሪያም ነበረቻት። ሦራም አብራምን፦ እነሆ፥ እንዳልወልድ እግዚአብሔር ዘጋኝ፤ ምናልባት ከእርስዋ በልጅ እታነጽ እንደ ሆን ወደ እርስዋ ግባ አለችው። አብራምም የሦራን ቃል ሰማ። አብራምም በከነዓን ምድር አሥር ዓመት ከተቀመጠ በኋላ፥ የአብራም ሚስት ሦራ ግብፃዊት ባሪያዋን አጋርን ወስዳ ለባልዋ ለአብራም ሚስት ትሆነው ዘንድ ሰጠችው። አጋርም ለአብራም ወንድ ልጅን ወለደችለት፤ አብራምም አጋር የወለደችለትን የልጁን ስም እስማኤል ብሎ ጠራው። አጋር እስማኤልን ለአብራም በወለደችለት ጊዜ አብራም የሰማንያ ስድስት ዓመት ሰው ነበረ» (ኦሪት ዘፍጥረት 16፡1-3፥ 15፥16)።

ቁርአን ውስጥ ያለውንስ ብናነብ ምን ይላል?

እስማኤል የተወለደው በአብርሃም የሸምግልና ዘመን መሆኑን ቁራአን የጻፈውን ብንመለከት:-

> ለዚያ ከሽምግልና በኋላ ኢስማዔልን፣ ኢስሐቅንም ለኔ ለሰጠኝ አላህ ምስጋና ይገባው፤ ጌታዬ ልመናን በእርግጥ ሰሚ ነውና፤» (ምዕራፍ 14 ኢብራሂም 39)

## 3. እስማኤልንና ይስሐቅን አስመልክቶ እግዚአብሔር ለአብርሃም የገባለት የተለያዩ የተስፋ ቃል ኪዳኖች

በመጽሐፈ ቶራኽ ውስጥ ምን ተጽፏል?

እግዚአብሔር በረከቱ ለእስማኤል ይደርሰው ዘንድ ቃል ገባ፤ ቃል ኪዳኑንም ከይስሐቅ ጋር መሠረተ። ይህን አስመልክቶ ብሉይ ኪዳን እንዲህ ይላል:-

> «አብራምም የዘጠና ዘጠኝ ዓመት ሰው በሆነ ጊዜ እግዚአብሔር ለአብራም ተገለጠለትና:- እኔ ኤልሻዳይ ነኝ፤ በፊቴ ተመላለስ፥ ፍጹምም ሁን፤ የሚስትህን የሦራን ስም ሦራ ብለህ አትጥራ፥ ስምዋ ሣራ ይሆናል እንጂ። እባርካታለሁ፥ ደግሞም ከእርስዋ ልጅ እሰጥሃለሁ፤ እባርካትማለሁ፥ የአሕዛብም እናት ትሆናለች፤ የአሕዛብ ነገሥታት ከእርስዋ ይወጣሉ። አብርሃምም በግንባሩ ወደቀ፥ ሳቀም፥ በልቡም አለ:- የመቶ ዓመት ሰው በውኑ ልጅ ይወልዳልን? ዘጠና ዓመትም የሆናትም ሣራ ትወልዳለችን? አብርሃምም እግዚአብሔርን:- እስማኤል በፊትህ ቢኖር በወደድሁ ነበር አለው።
>
> እግዚአብሔርም አለ:- በእውነት ሚስትህ ሣራ ወንድ ልጅን ትወልድልሃለች፥ ስሙንም ይስሐቅ ብለህ ትጠራዋለህ፤ ከእርሱ በኋላ ለዘሩ የዘላለም ቃል ኪዳን እንዲሆን ቃል ኪዳኔን ከእርሱ ጋር አቆማለሁ።
>
> ስለ እስማኤልም ሰምቼሃለሁ፤ እነሆ ባርኬዋለሁ፥ ፍሬያምም አደርገዋለሁ፥ እጅግም አበዛዋለሁ፤ አሥራ ሁለት አለቆችንም ይወልዳል፥ ታላቅ ሕዝብም እንዲሆን አደርገዋለሁ።
>
> ቃል ኪዳኔን ግን በሚመጣው ዓመት በዚሁ ጊዜ ሣራ ከምትወልድልህ ከይስሐቅ ጋር አቆማለሁ።



> ንግግሩንም ከእርሱ ጋር በፈጸመ ጊዜ እግዚአብሔር ከአብርሃም ተለይቶ ወጣ።» (ኦሪት ዘፍጥረት 17:1፥15-22)።

በቁርአንስ የተጻፈው ምን ይላል?

እግዚአብሔር ለእስማኤል የገባለትን የበረከት ቃልና ከይስሐቅ ጋር የመሠረተውን ቃል ኪዳን በተመለከተ በቁርአን አልተጠቀሱም።

## 4. ለአብርሃምና ለሚስቱ በመልእክተኞች በኩል የደረሰ የእግዚአብሔር የተስፋ ቃል

በዚሁ ላይ ቶራኽ ምን ይላል?

አሁንም እግዚአብሔር ለአረጋውያኑ ለአብርሃም እና ለባለቤቱ ሣራ በሽምግልና ዕድሜያቸው ይስሐቅን እንደሚሰጣቸው ቃል የገባላቸውን እንመለከታለን።

> «በቀትርም ጊዜ እርሱ በድንኳኑ ደጃፍ ተቀምጦ ሳለ እግዚአብሔር በመምሬ የአድባር ዛፍ ተገለጠለት። ዓይኑንም አነሣና እነሆ፥ ሦስት ሰዎች በፊቱ ቆመው አየ፤ ባያቸውም ጊዜ ሊቀበላቸው ከድንኳኑ ደጃፍ ተነሥቶ ሮጠ፥ ወደ ምድርም ሰገደ፥ እንዲህም አለ:- አቤቱ፥ በፊትህስ ሞገስ አግኝቼ እንደ ሆነ ባሪያህን አትለፈኝ ብዬ እለምናለሁ፤ ጥቂት ውኃ ይምጣላችሁ፥ እግራችሁን ታጠቡ፥ ከዚህችም ዛፍ በታች ዕረፉ፤ ቁራሽ እንጀራም ላምጣላችሁ፥ ልባችሁንም ደግፉ ከዚያም በኋላ ትሄዳላችሁ፤ ስለዚህ ወደ ባሪያችሁ መጥታችኋልና። እነርሱም:- እንዳልህ አድርግ አሉት። አብርሃምም ወደ ድንኳን ወደ ሣራ ዘንድ ፈጥኖ ገባና:- ሦስት መስፈሪያ የተሰለቀ ዱቄት ፈጥነሽ አዘጋጂ፥ ለውሺውም፥ እንጎቻም አድርጊ አላት። አብርሃምም ወደ ላሞቹ ሮጠ፥ እጅግ የሰባም ታናሽ ጥጃ ያዘና ለብላቴናው ሰጠው፥ ያዘጋጅም ዘንድ ተቻኰለ። እርጎና ወተትም ያዘጋጀውንም ጥጃ አመጣ፥ በፊታቸውም አቀረበው፤ እርሱም ከዛፉ በታች በፊታቸው ቆሞ ነበር፥ እነርሱም በሉ።
>
> እነርሱም:- ሚስትህ ሣራ ወዴት ናት? አሉት። እርሱም:- በድንኳኑ ውስጥ ናት አላቸው። እርሱም:- የዛሬ ዓመት እንደ ዛሬው ጊዜ ወደ አንተ በእውነት እመለሳለሁ፤ ሚስትህ ሣራም ልጅን ታገኛለች አለ።

ሣራም በድንኳን ደጃፍ በስተ ኋላው ሳለች ይህንን ሰማች። አብርሃምና ሣራም በዕድሜአቸው ሸምግለው ፈጽመው አርጅተው ነበር፤ በሴቶች የሚሆነውም ልማድ ከሣራ ተቋርጦ ነበር። ሣራም በልብዋ እንዲህ ስትል ሳቀች፦ ካረጀሁ በኋላ በውኑ ፍትወት ይሆንልኛልን? ጌታዬም ፈጽሞ ሸምግሎአል። እግዚአብሔርም አብርሃምን አለው፦ ካረጀሁ በኋላ በውኑ እወልዳለሁን? ስትል ሣራ ለምን ሳቀች? በውኑ ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር አለን? የዛሬ ዓመት እንደዛሬው ጊዜ ወደ አንተ እመለሳለሁ፤ ሣራም ልጅን ታገኛለች።» (ኦሪት ዘፍጥረት 18፥1-14)።

በቁርአን ውስጥ ምን ይላል?

አሁንም አረጋውያኑ ይስሐቅን እንደሚያገኙ ቃል ሲገቡላቸው እናያለን። እንዲህም ይነበባል፦

«መልክተኞቻችንም ኢብራሂምን በ(ልጅ) ብሥራት በእርግጥ መጡት፤ ሰላም አሉት፤ ሰላም አላቸው፤ ጥቂትም ሳይቆይ ወዲያውኑ የተጠበሰን የወይፈን ስጋ አመጣ። እጆቻቸውም ወደርሱ የማይደርሱ መሆናቸውን ባየ ጊዜ፥ ሳታቸው፤ ከእነሱም ፍርሃት ተሰማው፦ አትፍራ እኛ ወደ ሉጥ ሕዝቦች ተልከናልና አሉት። ሚስቱም የቆመች ስትሆን (አትፍራ አሉት) ሳቀችም፤ በኢስሐቅም አበሰርናት፤ ከኢስሐቅም በኋላ (በልጁ) በያዕቆብ (አበሰርናት)። (እርሷም) ዋልኝ! እኔ አሮጊት፥ ይህም ባሌ ሽማግሌ ኾኖ ሳለ እወልዳለሁን? ይህ በእርግጥ አስደናቂ ነገር ነው አለች፤፦ ከአላህ ትእዛዝ ትደነቂያለሽን? የአላህ ችሮታና በረከቶቹ በናንተ በኢብራሂም ቤተሰቦች ላይ ይኹኑ፥ እርሱ ምስጉን ሊጋስ ነውና አሉ።» (ምዕራፍ 11 ሁድ 69-73)።

## 5. የይስሐቅ መወለድ

ይህንን በተመለከተ በቶራኽ የተጻፈው ምን ይላል?

ይስሐቅ አባቱ አብርሃም የመቶ ዓመት ሽማግሌ ሲሆነው ተወለደ። ይህንን በተመለከተ ከቶራኽ ሲነበብ፦

«እግዚአብሔርም እንደተናገረው ሣራን አሰበ፤ እግዚአብሔርም እንደተናገረው ለሣራ አደረገላት። ሣራም ፀነሰች፥ እግዚአብሔርም በተናገረው ወራት ለአብርሃም በእርጅናው ወንድ ልጅን ወለደችለት። አብርሃምም የተወለደለትን ሣራ የወለደችለትን የልጁን



ስም ይስሐቅ ብሎ ጠራው። አብርሃምም ልጁ ይስሐቅ በተወለደለት ጊዜ የመቶ ዓመት ዕድሜ ነበረ።» (ኦሪት ዘፍጥረት 21፥1-3፤ 5)።

ቁርአንስ ስለዚሁ ምን አስፍሯል?

ይስሐቅ በአብርሃም የሽምግልና ዘመን መወለዱን አረጋግጦ ሲናገር እንዲህ ይላል፦

«ለዚያ ከሽምግልና በኋላ ኢስማዒልን፥ ኢስሐቅንም ለኔ ለሰጠኝ አላህ ምስጋና ይገባው፤ ጌታዬ ልመናን በእርግጥ ሰሚ ነውና!» (ምዕራፍ 14 ኢብራሂም 39)።

## 6. የአጋር ከነልጅዋ ከቤት መባረር

ቶራኽ በዚሁ ላይ ምን የመዘገበው አለው?

አጋር ከነልጅዋ ከቤት ተባረረች፦

«ሕፃኑም አደገ፥ ጡትንም ከመጥባት ተቋረጠ፤ አብርሃምም ይስሐቅን ጡት ባስጣለበት ቀን ትልቅ ግብዣ አደረገ። ሣራም ግብፃዊቱ አጋር ለአብርሃም የወለደችለትን ልጅ ሲስቅ አየችው። አብርሃምንም፦ ይህችን ባሪያ ከነልጅዋ አሳድድ፤ የዚህች ባሪያ ልጅ ከልጄ ከይስሐቅ ጋር አይወርስምና አለችው። ይህም ነገር በአብርሃም ዘንድ ስለ ልጁ እጅግ ችግር ሆነበት። እግዚአብሔርም አብርሃምን አለው፦ ስለ ባሪያህና ስለብላቴናው አትዘን፤ ሣራም የምትነግርህን ቃል ሁሉ ስማ፤ በይስሐቅ ዘር ይጠራልሃልና። የባሪያይቱን ልጅ ደግሞ ሕዝብ አደርገዋለሁ፥ ዘርህ ነውና። አብርሃም ማልዶ ተነሣ፥ እንጀራንም ወሰደ፥ የውኃ አቁማዳንም ለአጋር በትከሻዋ አሸከማት፥ ብላቴናውንም ሰጥቶ አሰወጣት፤ እርስዋም ሄደች በቤርሳቤህም ምድረ በዳ ተቅበዘበዘች። ውኃውም ከአቁማዳው አለቀ፤ ብላቴናውንም ከአንድ ቍጥቋጦ በታች ጣለችው፤ ፊት ለፊትም ተቀመጠች፥ ቃልዋንም አሰምታ አለቀሰች። እግዚአብሔርም የብላቴናውን ድምፅ ሰማ፤ የእግዚአብሔርም መልአክ ከሰማይ አጋርን እንዲህ ሲል ጠራት፦ አጋር ሆይ ምን ሆንሽ? እግዚአብሔር የብላቴናውን ድምፅ ባለበት ስፍራ ሰምቶአልና አትፍሪ። ተነሺ ብላቴናውንም አንሺ፥ እጅሽንም በእርሱ አሸፒው፤ ትልቅ ሕዝብ አደርገዋለሁና። እግዚአብሔርም ዓይንዋን ከፈተላት፥ የውኃ ጕድጓድንም አየች፤ ሄዳም አቁማዳውን በውኃ ሞላች፥

ብላቴናውንም አጠጣች። እግዚአብሔርም ከብላቴናው ጋር ነበረ፤ አደገም፥ በምድረ በዳም ተቀመጠ፥ ቀስተኛም ሆነ» (ኦሪት ዘፍጥረት 21 ፡8-15፤ 17-20)።

ቁርአንስ ስለዚሁ ጉዳይ ምን ይላል?

ቁርአን አጋር ከነልጅዋ ከቤት ስለመባረርዋ የዘገበው አንዳችም ነገር የለም።

### የእስማኤል ቤተ ሰቦችና የዘር ሐረግ

አብርሃምና አጋር
|
እስማኤል
|
ዐረቦች
|
መሐመድ

እስማኤልን አስመልክቶ እግዚአብሔር ለአብርሃም የገባለት ቃል፡-

«ስለ እስማኤልም ሰምቼሃለሁ፤ እነሆ ባርኬዋለሁ፥ ፍሬያማም አደርገዋለሁ፥ እጅግም አበዛዋለሁ፤ አሥራ ሁለት አለቆችንም ይወልዳል፥ ታላቅ ሕዝብም እንዲሆን አደርገዋለሁ» (ኦሪት ዘፍጥረት 17፡20)።

እግዚአብሔር ቃሉን የሚጠብቅ ታማኝ ነውና እስማኤል እንደ እግዚአብሔር ቃል አሥራ ሁለት ወንድ ልጆችን አግኝቶ እንመለከታለን።

ቶራኽ የዘገበው ሲነበብ፡- «የሣራ ባሪያ ግብፃዊቱ አጋር ለአብርሃም የወለደችው የአብርሃም ልጅ የእስማኤል ትውልድ ይህ ነው፤ የእስማኤልም የልጆቹ ስም በየስማቸውና በየትውልዳቸው እንዲህ ነው፤ የእስማኤል የበኩር ልጁ ነባዮት፥ ቄዳር፥ ነብዳኤል፥ መብሳም፥ ማስማዕ፥ ዱማ፥ ማሣ፥ ኩዳን፥ ቴማን፥ ኢጡር፥ ናፊስ፥ ቄድማ። የእስማኤል ልጆች እነዚህ ናቸው፥ ስማቸውም በየመንደራቸውና በየሰፈራቸው ይኸው ነው፤ በየወገናቸውም አሥራ ሁለት አለቆች ናቸው» (ኦሪት ዘፍጥረት 25፡12-16)።

ምንም እንኳ ከእስማኤል ዘር የተገኙ አገሮች በሙሉ በረከቱ ይደርሳቸው ዘንድ እግዚአብሔር የገባው ቃል ባይኖርም ዘሩ የበዛና የተብዛዛ እንዲሆን ለእስማኤል



የገባለትን ቃል ፈጽሟል። በዚህም የዚህ ሁሉ አገሮች ሕዝብ አባት እንዲሆን አብቅቶታል። ዓለምን በብዙ ሚልዮን ያጥለቀለቀው የዓረብ ሕዝብ የእግዚአብሔር ቃል ለመፈጸሙ በቂና ግልፁ ማስረጃ ነው።

ስለዚህም ዓረቦች የእስማኤል ዘሮች ናቸው፤ መሐመድ ደግሞ በፊናው የዓረቦች ዘር ነው። ይህ የዘር ሰንሰለት መሐመድን የእሥማኤል ዘር ያደርገዋል።

### የይስሐቅ ቤተሰብና የዘር ሐረግ

አብርሃምና ሣራ
|
ይስሐቅ
|
አይሁዳውያን
|
ኢየሱስ

እግዚአብሔር ይስሐቅን አስመልክቶ ለአብርሃም የገባለት ቃል ኪዳን፡-

«እግዚአብሔርም አለ፡- በውነት ሚስትህ ሣራ ወንድ ልጅን ትወልድልሃለች፥ ስሙንም ይስሐቅ ብለህ ትጠራዋለህ፤ ከእርሱ በኋላ ለዘሩ የዘላለም ቃል ኪዳን እንዲሆን ቃል ኪዳኔን ከእርሱ ጋር አቆማለሁ» (ኦሪት ዘፍጥረት 17፡19)።

እግዚአብሔር በገባው ቃል ኪዳን መሠረት ለአብርሃም፥ ለይስሐቅና ለያዕቆብ የገባው ቃል እንዲህ ይላል፡-

«የምድር አሕዛብ ሁሉም በዘርህ ይባረካሉ» (ኦሪት ዘፍጥረት 22፡18፤ 26፡4፤ 28፡14)።

እግዚአብሔር ለመላ አሕዛብ ቃል የገባለት ይህ በረከት በእምነት ብቻ የሚገኝ መዳን ነው። ሐዋርያው ጳውሎስ በኢንጅል ውስጥ እንዲህ ጽፏል፡-

«መጽሐፍም እግዚአብሔር አሕዛብን በእምነት እንዲያጸድቅ አስቀድሞ አይቶ፡- በአንተ አሕዛብ ሁሉ ይባረካሉ ብሎ ወንጌልን ለአብርሃም አስቀድሞ ሰበከ።» (ገላትያ 3፡8)።

ኢየሱስም በእምነት ብቻ የሚገኝ መዳንን አስመልክቶ የተናገረውን ከኢንጅል ብናነብ፡-

«...መዳን ከአይሁድ ነውና...» (ዮሐንስ 4፡22)።

የተገለጠው ይህ መዳን የተገኘው ከአይሁድ ዘር በሆነው በመሢሑ ኢየሱስ ነው።

ሐዋርያው ጳውሎስ በኢንጅል ውስጥ እንዲህ ጽፏል፦ «ለአብርሃምና ለዘሩም የተስፋው ቃል ተነገረ። ስለ ብዙዎች እንደሚነገር፦ ለዘሮቹም አይልም፤ ስለ አንድ እንደሚነገር ግን፦ ለዘርህም ይላል፥ እርሱም ክርስቶስ» (ገላትያ 3፡16)።

ኢየሱስ ከትንሣኤ በኋላ ለሐዋርያቱ ያስገነዘበውን በኢንጅል እንዲህ ይላል፦

«ከእናንተ ጋር ሳለሁ በሙሴ ሕግና በነቢያት በመዝሙራትም ስለ እኔ የተጻፈው ሁሉ ይፈጸም ዘንድ ይገባል ብዬ የነገርኋችሁ ቃሌ ይህ ነው አላቸው። በዚያን ጊዜም መጻሕፍትን ያስተውሉ ዘንድ አእምሮአቸውን ከፈተላቸው፤ እንዲህም አላቸው፦ ክርስቶስ መከራ ይቀበላል በሦስተኛውም ቀን ከሙታን ይነሣል፥ በስሙም ንስሐና የኃጢአት ስርየት ከኢየሩሳሌም ጀምሮ በአሕዛብ ሁሉ ይሰበካል ተብሎ እንዲሁ ተጽፎአል» (ሉቃስ 24፡44-47)።



ውድ አንባቢ፤ ኢንጅል የሚያረጋግጥልህ ይናገሯል፦

«ኃጢአተኞችን ሊያድን ክርስቶስ ኢየሱስ ወደ ዓለም መጣ የሚለው ቃል የታመነና ሁሉ እንዲቀበሉት የተገባ ነው» (1ኛ ጢሞቴዎስ 1፡15)።

«ሰዎች ሁሉ ሊድኑና እውነቱን ወደ ማወቅ ሊደርሱ በሚወድ በእግዚአብሔር በመድኃኒታችን ፊት መልካምና ደስ የሚያሰኝ ይህ ነው። አንድ እግዚአብሔር አለና፥ በእግዚአብሔርና በሰውም መካከል ያለው መካከለኛው ደግሞ አንድ አለ፥ እርሱም ሰው የሆነ ክርስቶስ ኢየሱስ ነው፤ ራሱንም ለሁሉ ቤዛ ሰጠ» (1ኛ ጢሞቴዎስ 2፡4-6)።

«እኛ በእርሱ ሆነን የእግዚአብሔር ጽድቅ እንሆን ዘንድ ኃጢአት ያላወቀውን እርሱን ስለ እኛ ኃጢአት አደረገው» (2ኛ ቆሮንቶስ 5፡21)።

«ክርስቶስ ደግሞ ወደ እግዚአብሔር እንዲያቀርበን እርሱ ጻድቅ ሆኖ ስለ ዓመፀኞች አንድ ጊዜ በኃጢአት ምክንያት ሞቶአልና፤ በሥጋ ሞተ በመንፈስ ግን ሕያው ሆነ» (1ኛ ጴጥሮስ 3፡18)።

«በዚህ ምክንያት ደግሞ እግዚአብሔር ያለ ልክ ከፍ ከፍ አደረገው፥ ከስምም ሁሉ በላይ ያለውን ስም ሰጠው፤ ይህም በሰማይና በምድር ከምድርም በታች ያሉት ሁሉ በኢየሱስ ስም ይንበረከኩ ዘንድ፥ መላስም ሁሉ ለእግዚአብሔር አብ ክብር ኢየሱስ ክርስቶስ ጌታ እንደ ሆነ ይመሰክር ዘንድ ነው» (ፊልጵስዩስ 2፡9-11)።

ልብ በል፡-

መሢሑ ኢየሱስን እንደ አዳኝህና ጌታህ ትቀበለው ዘንድ የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው። ኢየሱስን እንደ አዳኝህ በተቀበልከው ጊዜ ለመላ ኃጢአትህ ይቅርታን ታገኛለህ። እግዚአብሔርም ሰማያዊ አባትህ መሆኑን ትገነዘባለህ። በአብርሃም በይስሐቅና በያዕቆብ ዘርም እግዚአብሔር የገባውን የመዳን ቃል ኪዳን ታገኛለህ። መንግሥተ ሰማያትንም የምትወርስበት ዋስትና ታገኛለህ። መሢሑ ኢየሱስን እንደ ግል አዳኝህ ለመቀበል ከወሰንክ የሚከተለውን ጸሎት መጸለይ ትችላለህ። እግዚአብሔርም ጸሎትህን ይሰማል።

ኃያሉ አምላክ ሆይ፥ የአብርሃም፥ የይስሐቅና የያዕቆብ ዘር የሆነውን መሢሑ ኢየሱስን፥ ልክ እንደገባህልን ቃል ወደ ዓለም ስለላክልን አመሰግንሃለሁ። በላክኸው በመሢሑ ኢየሱስ በኩልም ለእኔ ያለህን ፍቅር ግልጥ አድርገህ ስለ አሳየኸኝ አመሰግንሃለሁ። ለኃጢአቴ ይቅርታም መሢሑ ኢየሱስ ሕይወቱን በመስቀል ላይ አሳልፎ ስለሰጠ አመሰግንሃለሁ። የዘለዓለም ሕይወት ይኖረኝ ዘንድ፥ መሢሑ ኢየሱስ ሞትን አሸንፎ ከመቃብር በመነሣቱ አመሰግንሃለሁ። ኃጢአተኛ መሆኔን አውቃለሁ። ለኃጢአቴም ይቅርታን እጠይቃለሁ። ለእኔ ሲል የገዛ ሕይወቱን አሳልፎ በሰጠው በመሢሑ ኢየሱስ የምትሰጠኝን ይቅርታ በዚህ ሰዓት እቀበላለሁ። ጌታዬ ይሆን ዘንድ ፍላጎቴ ነው። እግዚአብሔር ሆይ፥ ኢየሱስ ለእኔ ያለውን ፍቅር ያህል ሌሎችን እወድ ዘንድ እርዳታህ አይለየኝ። ኃጢአቴን ከእኔ ስላነሣህ አመሰግንሃለሁ። ስለተቀበልከኝም አመሰግንሃለሁ። ይህንንም ሁሉ ጌታዬና አዳኜ በሆነው በመሢሑ ኢየሱስ ስም እለምንሃለሁ። አሜን።